https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሠ/መ/ቁጥር 193392

ሐምሌ 28 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡-ክብሮም ደስታ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ

ተጠሪ ፡- ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከመንግስት ግዥ ጋር በተያያዘ የወጣ ጨረታ የሚሰረዝበትን የሕግ አግባብ የሚመለከት ነዉ፡፡አመልካች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የመንግስት ግዥ አፈጻጸም እና ንብረት አወጋገድ አቤቱታ አጣሪና ዉሳኔ ሰጪ ቦርድ ዘንድ በተጠሪ ላይ ባቀረበዉ አቤቱታ ተጠሪ በምጻእ ወርቂ ካምፓስ የመሰረተ ልማት ግንባታ ለማሰራት ባወጣዉ ጨረታ ላይ አመልካች የጨረታዉ አሸናፊ እንደሆንኩ በመግለጽ አመልካች ዉል እንድገባ ተጠሪ ከጠየቀኝ በኋላ ተጫራቾቹን ሲገመግም በአማካሪ ካስጠናዉ የምህንድስና ግምት ዋጋ (Engineering Estimation) መሰረት በማነጻጸር መገምገም ሲገባዉ አንደኛ የወጣሁትን ተጫራች ሁለተኛ ከወጣዉ ተጫራች ጋር በማነጻጸር የዋጋ ልዩነት አለ ማለቱ፣በጨረታ ሰነዱ ላይ ለቴክኒካል ግምገማዉ 80% እና ለፋይናንሻል ግምገማ 20% እንደሚያዝ ባስቀመጠዉ መሰረት አሸናፊዉ ድርጅት የሚመርጠዉ ዝቅተኛ ዋጋ በማቅረቡ ሳይሆን በጨረታ ሰነዱ፣በመንግስት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 16.19.2.1/ለ መሰረት ከዋጋ ባለፈ የሚታይ የተሻለ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እሴት መግለጫ በሆኑት የተወዳዳሪዉ ቴክኒካዊ የብቃት መስፈርቶች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምዛና ዉጤት ተጫራቾቹ ካቀረቡት ዋጋ ጋር አንድ ላይ ሲደመር በሚገኝ ጠቅላላ ድምር ዉጤት መሆኑን፤ሁለተኛ የወጣዉ ተጫራች በቴክኒካል ግምገማ 64.5%ቢያገኝም ዉጤት ከታወቀ በኂላ ለተጠሪ ቅሬታ ሲያቀርብ ነጥብ ተጨምሮ 69.29 ነጥብ እንዲሆን የተደረገበት መንገድ አግባብ ካለመሆኑም በላይ ድርጅቱ በተሰጠዉ ዉሳኔ ረክቶ አቤቱታ ባላቀረበበት ከቴክኒካል ግምገማ ዉጤት በኂላ በርከት ያለ ነጥብ ስለተጨመረለት በሚሉ ምክንያቶች አሸናፊ መሆኔ ከተገለጸ በኂላ ጨረታዉን መሰረዙ ተገቢ ስላልሆነ ከተጠሪ ጋር ዉል በመዋዋል ሥራዉን መስራት እንድችል ትእዛዝ ይሰጥልኝ በማለት አቤቱታዉን አቅርቧል፡፡

ተጠሪ ለቦርዱ ባቀረበዉ መልስ ከአመልካች ጋር ዉል እስካልተፈጸመ ድረስ ለአሸናፊ ተጫራች የአሸናፊነት ዉጤት በደብዳቤ መግለጹ አስገዳጅ ስላልሆነ አመልካች ተጠሪ ዉል እንዲዋዋል የሚገደድበት የሕግ አግባብ የለም፡፡በጨረታ ማስታወቂያዉ ላይ ተጠሪ ጨረታዉን በሙሉም ሆነ በመከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ እንደሆነ የገለጸ በመሆኑ ፣በግዥ አዋጅ አንቀጽ 41/1 እና በፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥር 3168/1 መሰረት ተጠሪ ዉል ከመፈረሙ በፊት በማንኛዉም ጊዜ ጨረታዉን የመሰረዝ መብት ያለዉ በመሆኑ ጨረታዉን የሰረዘዉ በሕግ አግባብ ነዉ፡፡የምህንድስና ግምቱ ብር 156,915,360.00 ሲሆን በጨረታ ሰነዱ የተጠየቀዉ ደረጃ GC-3 እና ከዚያ በላይ በማለት የወጣ መሆኑ ተጫራቾችን የሚገድብ በመሆኑ GC-4 እና ከዚያ በላይ እስከ ብር 185,000,000.00 በሚል ጨረታዉ ሊወጣ የሚገባ በመሆኑ ጨረታዉ ተሰርዧል፡፡ሁለተኛ የወጣዉ ተጫራች ቅሬታ አቅርቦ 18 ነጥብ ያህል የቴክኒካል ዉጤት መጨመሩ በአካሄድ የጎላ ችግር የነበረ መሆኑን ያሳያል፡፡እንዲሁም ጨረታ የወጣበት የግንባታ ሥራ ዉስብስብነት እና የተለያየ ሞያና ማሽነሪ የሚጠይቅ ስላልሆነ 80% ለቴክኒካል 20% ለፋይናንሻል ተብሎ ጨረታዉ መዉጣቱ ሁለት የቴክኒካል መስፈርት የሚያሟሉ ተጫራቾች የሰፋና የተጋነነ የፋይናንስ ልዩነት መፍጠር የቻለ በመሆኑ ጨረታዉ ተሰርዞ በድጋሚ ቢወጣ አግባብ በመሆኑ የተወሰደ እርምጃ ስለሆነ አቤቱታዉ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት መልሱን ሰጥቷል፡፡

ቦርዱም ከላይ በተመለከተዉ መሰረት የቀረበዉን የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በቁጥር መባኤ/አ-22/16/1489 በቀን 18/03/2010ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ምንም እንኳን ተጠሪ በጨረታዉ አንደኛ የወጣዉ አመልካች ሁለተኛ ከወጣዉ ተጫራች ጋር በማነጻጸር ያለዉን የዋጋ ልዩነት እንዲሁም ሁለተኛ የወጣዉ ተጫራች ቅሬታ አቅርቦ 18 ነጥብ ያህል የቴክኒካል ዉጤት መጨመሩ በአካሄድ የጎላ ችግር የነበረ መሆኑን ያሳያል በሚል ምክንያት ጨረታዉን መሰረዙ የሕግ አግባብ የሌለዉ ነዉ፡፡ሆኖም ተጠሪ በምላሹ እንደገለጸዉ የግምገማ ዘዴዉ ለቴክኒክ 80% ለዋጋ ደግሞ 20% መስጠቱ ስህተት የተደረገ መሆኑንና በተጫራቾች መካከል ሰፊ የዋጋ ልዩነት ለመፈጠሩ ምክንያት ነዉ ብሎ ካሰበና ይህን ከግምት በማስገባት ወደፊት ጨረታ ሲያወጣ በዚሁ ጨረታ ላይ ለቴክኒክ እና ለዋጋ ዉድድር የተሰጠዉን ክብደት በመጨመር ወይም በመቀነስ የተፈጠረዉን ችግር ለማስተካከል በማሰብ በመሆኑ፤በጨረታዉ የተሳተፉ ተጫራቾች ደረጃ 3 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ተቋራጮች በመሆናቸዉ ምክንያት በጨረታዉ ዉጤት ላይ ተጽእኖ አሳድሯል ወይም በዚህ ጨረታ ደረጃ 4 እና ከዚያ በላይ በሚል ተጨራቾች ተጋብዘዉ ቢሆን ኖሮ የዉጤት ለዉጥ ያመጣ ነበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብሎ በማሰብ እንደሆነ፤ምንም እንኳን ተጠሪ አመልካች የጨረታዉ አሸናፊ መሆኑን ገልጾ ዉል እንዲገባ በደብዳቤ ቢያሳዉቅም ዉል ከመፈረሙ በፊት ተጠሪ ጨረታዉን በሙሉ ወይም በከፊል መሰረዝ እንደሚችል ዩኒቨርሲቲዉ ጨረታዉን መሰረዙ በግዥ አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 30(1/ሀ) ላይ በግዥ አካሄድ ላይ ዉጤቱን ሊያዛባ የሚችል ስህተት መፈጸሙ ከተረጋገጠ ጨረታዉን ዉድቅ ማድረግ ወይም መሰረዝ እንደሚቻል የተቀመጠዉን ድንጋጌ የተከተለ ነዉ በማለት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 205736 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 11/06/2011 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ ራሱ ባቋቋመዉ አካል የጨረታ ሂደቱ ከተጠናቀቀና አመልካች የጨረታዉ አሸናፊ ከሆነ በኋላ 2ኛ ከወጣዉ የጨረታ አሸናፊ ዉጤት አንጻር የዋጋ ልዩነት ተመልክቶ የተጫራቾች ደረጃ እና የቴክኒክ እና የፋይናንስ ምደባ ላይ ስህተት ፈጽሜያለሁ በማለት ጨረታዉ እንዲሰረዝ ማድረጉ፤ እንዲሁም ይህንኑ ዉሳኔ ቦርዱ ማጽደቁ በግዥ አዋጅ አንቀጽ 30(1/ሀ) ስር የተመለከተዉን ጨረታ ዉድቅ ማድረጊያ መስፈርት የማያሟላ ፣ ከድንጋጌዉ ጋር የማይጣጣም እና ጨረታዉን ዉድቅ ለማድረግ የሚበቃ ምክንያት ስላልሆነ ተጠሪ ጨረታዉን የሰረዘበትና ቦርዱም ይህንኑ ያጸደቀበት አግባብ በአዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 30(1/ሀ) ስር የተደነገገዉን የተከተለ ባለመሆኑ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ዉል ሊዋዋል ይገባል በማለት የቦርዱን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

በመቀጠል ተጠሪ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ይግባኝ አቅርቦ ችሎቱም በመ/ቁጥር 175066 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 28/08/2012ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ በግዥ መመሪያ ቁጥር 2/2002 ቁጥር 2.8 መሰረት ጨረታዉን ባወጣበት ወቅት ጨረታዉን መሰረዝ እንደሚችል ያሳወቀ በመሆኑና ጨረታዉን ለመሰረዝ መሰረት ያደረጋቸዉና በቦርዱ ዉሳኔ ላይ የተጠቀሱ ምክንያቶች ጨረታዉን ለመሰረዝ በቂ ነዉ፡፡ተጠሪ በግዥ አዋጅ ቁጥር 649/2009 አንቀጽ 30(1/ሀ-ረ) ስር ከተደነገጉት ምክንያቶች በአንዱ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ምክንያቶች ጨረታዉ መሰረዙን ከመግለጽ ባለፈ የምክንያቶቹን አግባብነት ማስረዳት አይጠበቅበትም፡፡ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ቦርዱ የሰጠዉን ዉሳኔ የግዥ አዋጁንና መመሪያዉን ያላገናዘበ ነዉ በማለት መሻሩ ተገቢ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ ሽሮ የቦርዱን ዉሳኔ አጽንቷል፡፡አመልካች በቀን 27/11/2012 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 30(1/ሀ-ረ) እና በመንግስት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 2.8.1.1 ስር በተዘረዘሩት አንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ምክንያቶች ብቻ ጨረታዉን መሰረዝ እንደሚችል፤በቂና አሳማኝ ምክንያቶች ሊኖሩት እንደሚገባ በፍርድ ሀተታዉ ላይ ከገለጸ በኋላ ተጠሪ የምክንያቶቹን አግባብነት ማስረዳት አይጠበቅበትም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የአዋጁን አንቀጽ 30ን በተሳሳተ መንፈስ በመተርጎም ነዉ፡፡እንዲሁም በግዥ መመሪያ ላይ የሌለ አንቀጽ 2.8.1.1 ደጋግሞ በመጥቀስ በአዋጁ አንቀጽ 5 ላይ የመንግስት ግዥ ስርዓት መርሆዎችን ወደ ጎን የተወ ዉሳኔ

ሰጥቷል፡፡ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ጨረታዉን ለማሰረዝ የሚያስችል በአዋጁ አንቀጽ 30(1/ሀ-ረ)ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ዉስጥ የሚወድቅ በቂና አሳማኝ ምክንያት መኖሩን ሳያረጋግጥ የሰጠዉ ዉሳኔ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡የመንግስት መስሪያ ቤት የጨረታ መሰረዣ ምክንያቶች በሚያሳዉቅበት ጊዜ ምክንያቶቹን ማስረዳት አይጠበቅባቸዉም ማለት እንጂ በዉሳኔዉ ቅር የተሰኙ ወገኖች በአስተዳደርና በፍርድ ቤት ቅሬታ ሳይቀርቡ ምክንያቶቹ በተጨባጭ የተፈጸሙ መሆናቸዉን ከአዋጁ አንቀጽ 30/1 አንጻር ሊረጋገጥ አይገባም ማለት እንዳልሆነ ከግምት ያላስገባ ዉሳኔ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ነዉ፡፡በመሆኑ የይግባኝ ሰሚዉ ችሎት እና የቦርዱ ዉሳኔ ተሽሮ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአዋጁ አንቀጽ 30(/ሀ) ላይ በግዥ አካሄድ ላይ ዉጤቱን ሊያዛባ የሚችል ስህተት መፈጸሙን የሚያረጋግጥ ከሚለዉ አስገዳጅ መስፈርት አንጻር ጉዳዩን አመዛዝና ጨረታዉ ሊሰረዝ አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ነዉ ተብሎ ይጽናልኝ በማለት አቤቱታዉን አቅርቧል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ለዉሉ መቋረጥ ተጠሪ የዘረዘራቸዉን ምክንያቶች በአዋጅ ዉስጥ የሚሸፈኑ መሆን አለመሆናቸዉን የስር ፍርድ ቤት አጣርቶ መወሰን አለመወሰኑን ተጠሪ ባለበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 25/02/2013 ዓ/ም የተፃፈ መልሱን ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ፡-በጨረታ ሰነዱ ላይ ተጠሪ ጨረታዉን በሙሉም ሆነ በከፊል መሰረዝ እንደሚችል በግልጽ ተመልክቷል፡፡ይህ ጨረታ የተሰረዘዉም በጨረታ ሰነዱ ላይ ተጠሪ ጨረታዉን በሙሉም ሆነ በከፊል መሰረዝ እንደሚችል አስቀድሞ በገለጸዉ መሰረት ነዉ፡፡ተጠሪ የጨረታዉን ዉጤት ለማጽናትም ሆነ ለመሰረዝ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3168/1 እና በአዋጅ ቁጥር 649/2001 መሰረት ሙሉ ነጻነት እንዳለዉ ተድንግጓል፡፡በተጨማሪም የዚህ ፕሮጀክት ሥራ ዉስብስብነት እና የተለየ ሙያና ማሽነሪ እምብዛም የማይጠይቅ ስለሆነ 80% ለቴክኒካል 20% ደግሞ ለፋይናንሻል ተብሎ ጨረታ መዉጣቱ ለመንግስት አዋጭ ካለመሆኑም በተጨማሪ ይህ ቀመር ተግባር ላይ ሲቀየር የተጋነነ የፋይናንስ ልዩነት የሚፈጥር ሆኖ በመገኘቱ፤ይህም ተጠሪ ለሌላ የልማት ሥራ ሊያወጣዉ የነበረዉን ገንዘብ እንዲያጣ ምክንያት ይሆናል፡፡የገንዘቡ ልዩነት የተጋነነ ስለሆነ ጨረታዉ ተሰርዞ አሳታፊ በሆነ መንገድ እንደአዲስ ጨረታ እንዲወጣ ማድረጉ የሕዝብና የመንግስት ጥቅም የሚያስጠብቅ ነዉ፡፡ሁለተኛ የወጣዉ ተጫራች ቅሬታ አቅርቦ 18 ነጥብ ያህል የቴክኒክ ዉጤት መጨመሩ በአካሄድ የጎላ ችግር የነበረ ስለመሆኑ ሌላ አመላካች ነጥብ ነዉ፡፡በመሆኑም ጨረታዉ መሰረዙ ተገቢ ነዉ ተብሎ በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካችም በቀን 23/03/2013 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በላይ በአጭሩ የተመለከተዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል የያዘዉን ጭብጥ በማሻሻል አመልካች የጨረታዉ አሸናፊ መሆኑ ከተገለጸ በኋላ ተጠሪ ጨረታዉን መሰረዙና ጨረታዉ መሰረዙ ተገቢ ነዉ ተብሎ በቅሬታ ሰሚ ቦርዱና በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በተሰጡ ዉሳኔዎች የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ተጠሪ በምጻአ ወርቂ ካምፓስ የመሰረተ ልማት ግንባታ ለማሰራት ባወጣዉ ጨረታ ላይ አመልካች የጨረታዉ አሸናፊ እንደሆነ ገልጾ ተጠሪ ለአመልካች ማሳወቁ በግራ ቀኙ የታመነ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ የአመልካች ክርክር ተጠሪ በምጻአ ወርቂ ካምፓስ የመሰረተ ልማት ግንባታ ለማሰራት ባወጣዉ ጨረታ ላይ አመልካች የጨረታዉ አሸናፊ እንደሆንኩ ገልጾ ዉል እንድዋዋል በደብዳቤ ከጠየቀኝ በኂላ ከግዥ አዋጅና መመሪያ ዉጭ የሆኑ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ አለአግባብ ጨረታዉን በመሰረዝ የወሰደዉ እርምጃ ዉድቅ ተደርጎ ከተጠሪ ጋር ዉል እንዲዋዋል ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡ተጠሪ ደግሞ ጨረታዉ የተሰረዘዉ በሕግ በተሰጠዉ ሥልጣንና በጨረታዉ ላይ ጨረታዉ በሙሉም ሆነ በከፊል ሊሰረዝ እንደሚችል ለተወዳዳሪዎች በተገለጸዉ መሰረት የመንግስት ግዥ አዋጅ እና መመሪያ ድጋፍ ባለዉ ምክንያት የተሰረዘ ጨረታ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካችን አቤቱታ በመጀመሪያ የተመለከተዉ የፌዴራል የመንግስት ግዥ አፈጻጸም እና ንብረት አወጋገድ አቤቱታ አጣሪና ዉሳኔ ሰጪ ቦርድ እና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጡት ዉሳኔ ተጠሪ ጨረታዉን የሰረዘዉ በሕግ አግባብ ነዉ በማለት ወስነዋል፡፡ በሌላ በኩል የቦርዱን ዉሳኔ በይግባኝ የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ጨረታዉን ዉድቅ ያደረገዉ ጨረታዉን ለመሰረዝ የሚያበቃ በአዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 30/1 ከተዘረዘሩ ምክንያቶች ጋር የተጣጣመ ምክንያት በሌለበት የተሰረዘ ጨረታ ስለሆነ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ዉል ሊዋዋል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡እኛም ተጠሪ አመልካች የጨረታዉ አሸናፊ መሆኑን ካሳወቀ በኂላ ጨረታዉን መሰረዙ ተገቢ ነዉ ተብሎ በመወሰኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አመልካች ጨረታዉን ለመሰረዝ የተጠቀመባቸዉን ምክንያቶች አግባብነት ካለዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ ተመልክተናል፡፡

የአስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ግዥ ከሚፈጽሙባቸዉ ዘዴዎች መካከል በግልጽ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ አንዱ ሲሆን የግልጽ ጨረታ ግዥ አፈጻጸም ሥርዓት በፌዴራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና አዋጁን ተከትሎ ከሰኔ 01 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ በፀናዉ የፌዴራል መንግስት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ እና ማኑዋል ላይ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡በአዋጁ አንቀጽ 5 ስር የመንግስት ግዥ አፈጻጸም እና ንብረት አስተዳደር ሂደት መከተል የሚገባ መርሆዎች ተደንግገዋል፡፡እነዚህም መርሆዎች በግዥ አፈጻጸም ረገድ የመንግስት ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለዉን ጥቅም ማስገኘት፣በአዋጁ በተፈቀደዉ ልዩ አስተያየት ካልሆነ በስተቀር በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል አድልዎ አለማድረግ፣ከግዥ ጋር በተያያዘ የሚሰጠዉ ዉሳኔ ግልጽ እና ፍትሐዊ መሆን እንዲሁም ዉሳኔዎችና የተወሰዱ እርምጃዎች ተጠያቂነት የሚያስከትሉ እንደሆኑ ተገንዝቦ መስራትን የሚጠይቁ ናቸዉ፡፡እነዚህን መርሆዎች ተከትሎ የግዥ አፈጻጸም ሂደቱን መምራት የግዥ አፈጻጸምን ዉጤታማ በማድረግ ለአገር ሁለንተናዊ እድገት የሚያበረክተዉ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ስለሆነ በአግባቡ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ግዥ የሚፈጽመዉ መስሪያ ቤት የጨረታዉን አሸናፊ ይፋ ከመደረጉ በፊት በማንኛዉም ጊዜ ጨረታዉን ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብት እንዳለዉ በጨረታ ሰነዱ ላይ መግለጽ እንደሚገባ በአዋጁ አንቀጽ 37/በ ላይ የተደነገገዉም የግልጽነትና

የተጠያቂነት መርሆዎች ተግባራዊ ከሚደረግባቸዉ መንገዶች ዉስጥ አንዱ መንገድ ሆኖ መታየት የሚችል ነዉ፡፡

በአዋጁ አንቀጽ 43/6 እና በመመሪያዉ አንቀጽ 16.8 ስር እንደተደነገገዉ ግዥ የሚፈጽመዉ የመንግስት መስሪያ ቤት የመጫረቻ ሰነድ መገምገም የሚችለዉ አስቀድሞ በጨረታ ሰነዱ ላይ በግልጽ በማሳየት ካስቀመጠዉ መስፈርቶች አንጻር ነዉ፡፡እነዚህን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ ግዥዉ የሚኖረዉን ጠቀሜታ ወይም ኢኮኖሚያዊ እሴት ሊወስኑ የሚችሉ መስፈርቶችን እና እያንዳንዱ መስፈርት የሚኖረዉን አንጻራዊ ክብደት በግልጽ በጨረታ ሰነዱ ላይ በማሳየትና በእነዚሁ መስፈርቶች ላይ የተመሰረተ የመጀመሪያ ደረጃ እና ዝርዝር ግምገማ በማካሄድ በአጠቃላይ ዉጤት (በሁለት ኤንቬሎፕ የቀረበ ጨረታ ከሆነ የግዥዉን የጠቀሜታ እሴት የሚወስኑ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ የቴክኒክና የፋይናንስ አጠቃላይ ግምገማ ድምር ዉጤት) ከፍተኛ ነጥብ ያገኘዉን ተወዳዳሪ መምረጥ እንደሚገባዉ በመመሪያዉ አንቀጽ 16.8.2.ለ እና 16.19.2.1.ለ ላይ ከተመለከተዉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የቀረበለትን የጨረታ ግምገማ ሪፖርት ተመልክቶ ግዥዉን እንዲያጸድቅ ሥልጣን የተሰጠዉ አካል የግምገማ ሪፖርቱን ሙሉ በሙሉ በመቀበል ቀጣይ አፈጻጸሞች እንዲከናወኑ መፍቀድ አሊያም የግምገማዉን ሪፖርት አለመቀበል እንደሚችል በመመሪያዉ አንቀጽ 16.23.2 ስር ተመልክቷል፡፡

በተጨማሪም በአዋጁ አንቀጽ 46/2 እና በመመሪያዉ አንቀጽ 16.24.2 እና 16.27.2 እንዲሁም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3168 ስር በጨረታዉ አሸናፊ ለሆነዉ ተጫራች የጨረታዉ አሸናፊ እንደሆነ ተገልጾ የሚላከዉ ድብዳቤ በመንግስት መስሪያ ቤቱ እና በተጫራቹ መካከል እንደዉል ሆኖ ሊያገለግል እንደማይችል ተደንግጓል፡፡በመንግስት መሥሪያ ቤቱ እና በተጫራቹ/በአቅራቢዉ መካከል ዉል እንደተፈጸመ የሚቆጠረዉ ዝርዝር ጉዳዮችን ያካተተ ዉል በመስሪያ ቤቱ ኃላፊና በተጫራቹ ሲፈረም ብቻ በመሆኑ የጨረታዉ አሸናፊ በመገለጹ ብቻ ዉል እንደተፈጸመ አይቆጠርም፡፡ይህም የሚያሳየዉ በፍትሐ ብሔር ሕግ በጠቅላላ የዉል ሕግ ድንጋጌዎች ከቁጥር 1681 እስከ 1695 ድረስ ባሉ ድንጋጌዎች መሰረት ተጠሪ አመልካች የጨረታዉ አሸናፊ እንደሆነ በማሳወቅ ዉል እንዲዋዋል ጥሪ ሲያደርግና አመልካችም የቀረበለትን ሀሳብ ተቀብሎ ዉል ለመዋዋል ሲቀርብ የዉል ሀሳብ በማቅረብ (Offer) እና የቀረበዉን ሀሳብ በመቀበል (Acceptance) በመካከላቸዉ ዉል ተቋቁሟል ለማለት የሚያስችል ሁኔታ እንዳለ ሊቆጠር ይችል ይሆናል፡፡ሆኖም ከሕዝብ አገልግሎት ሥራ ጋር የተያያዘ እና የአስተዳደር መሥሪያ ቤቱን ሥራ ተካፋይነት ቀጣይነት ባለዉ መልኩ የሚጠይቁ የመንግስት ግዥ ዉሎች እንደአስተዳደር ዉል የሚቆጠሩ ስለሆኑ የመንግስትና የሕዝብ ዉስን ሀብት ምክንያታዊ በሆነ አጭር ጊዜ ለታለመለት አላማ መዋሉን ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ሕጉ በልዩ ሁኔታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3167 እና 3168 የደነገገዉንና እና በግዥ ሕግጋት ላይ የተመለከተዉን መከተል ይገባል፡፡በዚህ መሰረት የአስተዳደር የግዥ ዉል ተቋቋመ ሊባል የሚችለዉ የጨረታዉ አሸናፊ በደብዳቤ አሳዉቆ አሸናፊዉ ጥሪዉን

ተቀብሎ በመቅረቡ ብቻ ሳይሆን በግዥ ሕግጋቱ በተመለከተዉ አግባብ ከተዋዋዮች የሚጠበቀዉ ተሟልቶ የዉሉ ጉዳይ በሚገባ አኳኋን ተጽፎ በመንግስት መስሪያ ቤቱና በጨረታዉ አሸናፊ ሲፈረም ብቻ ነዉ ፡፡

እንዲሁም የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ከጨረታዉ አሸናፊ ጋር የግዥ ዉል ከመፈራረማቸዉ በፊት በማንኛዉም ጊዜ ጨረታን፣የመወዳደሪያ ሀሳብን እና የዋጋ ማቅረቢያን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ዉድቅ ማድረግ የሚችሉባቸዉ ምክንያቶች በአዋጁ አንቀጽ 30/1 ስር በዝርዝር ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ስር ከተመለከቱት ምክንያቶች ዉስጥ አንዱ በሆነዉ በንኡስ አንቀጽ 1/ሀ ስር በግዥ አካሄድ ላይ ዉጤቱን ሊያዛባ የሚችል ስህተት መፈጸሙ ከተረጋገጠ ጨረታዉ፣የመወዳደሪያ ሀሳቡ ወይም የዋጋ ማቅረቢያዉ በሙሉ ወይም በከፊል ዉድቅ ሊደረግ እንደሚችል የተደነገገዉ ነዉ፡፡በዚህ እና በሌሎች በድንጋጌዉ በተመለከተዉ ምክንያት ጨረታዉ ሲሠረዝ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የምክንያቶቹን አግባብነት እንዲያስረዱ ባይገደዱም ጨረታዉ የተሰረዘበትን ምክንያት የሚገልጽ ማስታወቂያ ለእጩ ተወዳዳሪዉ ማድረስ እንዳለባቸዉ በአዋጁ አንቀጽ 30/2 ስር ተደንግጓል፡፡ይህም ድንጋጌ እጩ ተወዳዳሪዉ የምክንያቱን በቂ መሆን አለመሆን ወይም ተገቢ መሆን አለመሆን መስሪያ ቤቱ እንዲያስረዳዉ ማስገደድ እንደማይችል ነገር ግን መስሪያ ቤቱ የግልጽነት መርህን ተከትሎ ጨረታዉን የሰረዘበትን ምክንያት ማሳወቅ ብቻ እንደሚጠበቅበት የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡ይህ ማለት ግን ጨረታዉ የተሰረዘዉ በጨረታ ሰነዱ ላይ ከተቀመጡ መስፈርቶች እና ከሕግ አግባብ ዉጭ በሆኑ ምክንያቶች ነዉ የሚል ቅሬታ በእጩ ተወዳዳሪዎች በየደረጃዉ ለቅሬታ ሰሚ አስተዳደር አካል እና ለመደበኛ ፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ መሥሪያ ቤቱ ለማስረዳት አይገደደም ማለት እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ ተጠሪ በጨረታ ሰነዱ ላይ የግምገማ ዘዴዉ ለቴክኒክ 80% ለዋጋ ደግሞ 20% ዋጋ እንደሚሰጥ ተገልጾ በወጣዉ የጨረታ መስፍርት መሰረት ግምገማ ተደርጎ አመልካች አሸናፊ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ይህም የሚያሳየዉ የጨረታዉ ግምገማ አስቀድሞ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተቀመጠዉ መስፈርት መሰረት መገምገሙን የሚያሳይ ነዉ፡፡ተጠሪ ጨረታዉን ከሰረዘበት ምክንያች መካከል አንዱ ምክንያት የግንባታ ሥራዉ ዉስብስብነት የሌለዉ በመሆኑ የተለየ ሙያና ማሽነሪዎችን ብዙም የማይፈልግ ሆኖ እያለ በጨረታ ሰነዱ ላይ በስህተት ለቴክኒክ 80% ለፋይናንስ ደግሞ 20% ዋጋ እንደሚሰጥ ተገልጾ ጨረታ መዉጣቱ የተጋነነ የፋይናንስ ልዩነት እንደሚፈጥር ስለተረጋገጠ በዚህ ሁኔታ ዉል መዋዋሉ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ የለዉም የሚል ምክንያት ነዉ፡፡ ይህም ምክንያት በጨረታ አካሄድ የተፈጠረ ስህተት እንደሆነ የሚያሳይ ሲሆን አመልካች ምክንያቱ እንደስህተት ሊቆጠር የማይችል ስለመሆኑና ስህተቱም በጨረታ አካሄድ ስህተት የተፈጠረ አይደለም በማለት በማስረጃ አስደግፎ ለቦርዱም ሆነ ለስር ፍርድ ቤቶች ያቀረበዉ አሳማኝ

መከራከሪያ የለም፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ጨረታ የፋይናንሻል እና የቴክኒካል ሀሳብ የሚቀርብበት በመሆኑ በሁለት ኤንቨሎፕ የቀረበ ነዉ፡፡በሁለት ኤንቨሎፕ የሚቀርብ ጨረታ ላይ ግዥዉ የሚኖረዉን ጠቀሜታ ወይም ኢኮኖሚያዊ እሴት በጨረታ ሰነዱ ላይ የተቀመጠዉን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ የተጫራቹን ዉጤት በመወሰን አሸናፊዉን መለየት ወይም የጨረታዉን ዉጤት በማጽደቅም ዉል ወደ መፈጸሙ መግባት ወይም ዉል መግባቱ አዋጭ አይደለም የሚል ከሆነም የጨረታዉን ዉጤት ባለማጽደቅ ጨረታዉን መሰረዝ እንደሚቻል በመመሪያዉ አንቀጽ 16.8.2.ለ ፣ 16.19.2.1.ለ እና 16.23.2 ላይ ከተደነገገዉ ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተጨማሪም በጨረታዉ የተጋበዙት ተጫራቾች ደረጃ 3 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ተቋራጮች በመሆናቸዉ ምክንያት የጨረታዉ ዉጤት ጠቀሜታ ላይ ተጽእኖ እንዳሳደረና በጨረታዉ ላይ ደረጃ 4 እና ከዚያ በላይ በሚል ተቋራጮች ተጋብዘዉ ቢሆን ኖሮ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለዉ ዉጤት ይገኝ እንደነበር በመገንዘብ በዚህም ላይ ማስተካከያ ተደርጎ ጨረታ እንዲወጣ በማሰብ አመልካች አሸናፊ የሆነበትን ጨረታ መሰረዙም ከላይ እንደተመለከተዉ በአዋጁ አንቀጽ 30(1/ሀ) ማእቀፍ ዉስጥ የሚታይና ጨረታዉን ሊያሰርዝ የሚችል ምክንያት ነዉ፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪ በመንግስት ግዥ ሕግጋት በተመለከተዉ አግባብ እና በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3167 እና 3168 ስር በተደነገገዉ መሰረት ከጨረታዉ አሸናፊ ጋር የግዥ ዉል ከመፈራረሙ በፊት ጨረታዉን የመሰረዝ ሙሉ ነጻነት አለዉ፡፡ከላይ እንደተመለከተዉ ተጠሪ በጨረታ ሰነዱ አዘገጃጀት ሂደት የተፈጠረዉ ስህተት ታርሞ ለቴክኒክና ለፋይናንስ ዉድድር የተሰጠዉ መቶኛ ዋጋ ተቀንሶና ተጨምሮ ቢስተካከል እንዲሁም የጨረታዉ ተጋባዥ ተቋራጮች ደረጃም ተስተካክሎ የጨረታ ሰነድ ተዘጋጅቶ ሌላ ጨረታ ቢወጣ የሚገኘዉን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ከግምት በማስገባት ጨረታዉ እንዲሰረዝ መወሰኑ በግዥ አዋጅ አንቀጽ 30(1/ሀ) ስር በተደነገገዉ አግባብ በግዥ አካሄድ ላይ ከግንባታዉ የሚገኘዉን ጠቀሜታ(ዉጤት) የሚያዛባዉን ስህተት ለማረም እንደተወሰደ እርምጃ ተደርጎ የሚቆጠር ነዉ፡፡በመሆኑም ቦርዱ በእነዚህ ምክንያቶች መነሻ ጨረታዉ መሰረዙ ተገቢ ነዉ ብሎ የሰጠዉ ዉሳኔ ሕግን መሰረት ያደረገ ነዉ ከሚባል በስተቀር ሊታረም የሚችል ስህተት የተፈጸመበት አይደለም፡፡ይህንን ዉሳኔ በመሻር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ የመንግስት ግዥ በተመለከተ ተፈጻሚነት ባላቸዉ ከላይ በተጠቀሱ ሕግጋት ለማሳካት የተፈለገዉን ዓላማና የአዋጁን አንቀጽ 30(1/ሀ) ትክክለኛ አተገባበርን ያልተከተለ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ስህተት ነዉ፡፡እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በሻረበት ዉሳኔ ላይ የግዥ መመሪያዉ አንቀጽ እንደሆነ በመግለጽ የጠቀሰዉ አንቀጽ 2.8.1.1 በመመሪያዉ ላይ የሚገኝ ሳይሆን በአዋጁ አንቀጽ 78/3 ስር በተሰጠዉ ሥልጣን መሰረት የፌዴራል መንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ባወጣዉ የፌዴራል መንግስት ግዥ አፈጻጸም ማኑዋል ላይ ያለ አንቀጽ በመሆኑና ለተያዘዉም ጉዳይ አግባብነት ያለዉ በመሆኑ አንቀጽ በመሆኑ ከዚህ አኳያ በማየት የአመልካችን ክርክር አልተቀበልንም፡፡ሆኖም ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዉሳኔዉ ላይ ተጠሪ ጨረታዉን መሰረዙን ከመግለጽ ባለፈ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የምክንያቹን አግባብነት ማስረዳት አይጠበቅበትም በሚል ያሰፈረዉ ድምዳሜ በአዋጁ አንቀጽ 30/2 ላይ የተመለከተ ሀሳብ ቢሆንም በዉሳኔዉ ላይ እንደተመለከተዉ በድምዳሜ መልክ ሊቀመጥ የሚገባ ሳይሆን ሕጉ ይህንን በማለት ለማስተላለፍ የፈለገዉ ሀሳብ ምን እንደሆነ ተመላክቶ መቀመጥ የነበረበት በመሆኑ የፍርድ አጻጻፍ ጉድለት ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ቢሆንም ከዉጤት አንጻር ሲታይ ዉሳኔዉን የሚያስለዉጥ ሆኖ አላገኘነዉም፡፡በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የመንግስት ግዥ አፈጻጸም እና ንብረት አወጋገድ አቤቱታ አጣሪና ዉሳኔ ሰጪ ቦርድ በቁጥር መባኤ/አ-22/16/1489 በቀን 12/03/2010ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 175066 ላይ በቀን 28/08/2012 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ፀንተዋል፡፡

2. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

## <u>ት እ ዛ ዝ</u>

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ